በግብርና ሚኒስቴር

እንሰሳት ሀብት ዘርፍ

የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት

# የ2011 በጀት ዓመት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት

ሐምሌ **2011** ዓ.ም

# በእንስሳት ሀብት ዘርፍ
# የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት
# የ 2011 በጀት ዓመታዊ አፈጻጸም ሪፖርት

ደርሞ

የኤክስፖርት ቄራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን ዳይሬክቶሬት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚገነቡትን የኤክስፖርት ቄራዎች ከግንባታ ቦታ መረጣ ጀምሮ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ቄራዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁና ጥራት ያለው ምርት በማምረት እንዲልኩ የበኩሉን ከፍተኛ ዕገዛና ቁጥጥር ያደርጋል።

በመቀጠልም ቄራዎቹ የተቀባይ አገሮችን የቅበላ መስፈርት እንዲያሚሉ ተገቢውን ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የመላክ ፈቃድ እንዲያገኙ ይሠራል። የመላኪያ ፈቃድ ላገኙ ኤክስፖርት ቄራዎች የስጋ ምርመሪ ባለሙያዎችን በመመደብ አለም ዓቀፉን አሰራር እና የተቀባይ አገሮችን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ የኢንስፔክሽን እና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት በመስጠት ለአገራችን የሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ኤክስፖርት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል።

በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎችና ከተሞች ለሚገኙና ወደ ውጪ ሀገር ምርታቸውን ለመላክ ፈቃድ ላገኙ 11 ኤክስፖርት ቄራዎች (የተወሰኑት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ያቀርባሉ) ይህ አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪም የእንስሳትን ተረፈ ምርት በማቀነባበር ወደ ውጪ ለሚልኩ 10 ባለሀብቶች ተመሳሳይ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። በዚህ ዓመት የተወሰኑ ኤክ/ቄራዎች ምርታቸውን በተለያየ ወቅቶች ለመላክ ያልቻሉ ሲሆን እነሱም ኤልፎራ ደብረ ዘይት በእርጅናና የማቀዝቀዛ ክፍሎች የተበላሹ በመሆኑ (ከጥር ወር ጀምሮ በማስተካከል መላክ ጀምሯል)፣ የአበርገሌ ኤክ/ቄራ የዱባይን መስፈርት ባለሚሟላቱ ምክንያት የማይልክ ሲሆን ወደ ሳውዲ ግን መላክ እየቻለ በማናጅመንት ችግር ላለፉት አራት ዓመታት አላከናወነም፣ የጅግጅጋ ኤክ/ቄራ ከረመዳን ጾም ቦሃላ ማለትም ሀምሌ 2010 ዓ.ም ጀምሮ ለዕድሳትና ከተለያየ የማናጅመንት ችግርና ኤክስፖርቱ አዋጪ ባለመሆኑ ምክንያት በደብዳቤ ድርጅቱ ለተወሰነ ግዜ መዘጋቱንና ሰራተኛ መበተኑን አሳውቋል። ከዚህም በተጨማሪ ከመጋቢት ወር ጀምሮ የአክሽከር ኤክ/ቄራ ከጥገና ጋር ተያይዞ ለወራቶች እንደተዘጋ ቄራው ያሳወቀ በመሆኑ ከዚህ ወር ጀምሮ ኤክስፖርት ማድረግ ያልቻለ ሲሆን በነዚህ ምክንያቶች የአገራችን ሥጋ ምርት ኤክስፖርት መቀዛቀዝ አሳይቷል።

በዋና መ/ቤት ደረጃ ዳይሬክቶሬቱ በአብዛኛው በየቄራው የሚሰራውን የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን ሥራዎች የማስተባበር፣ በየደረጃው ያለውን የእውቀት የክህሎትና የግብዓት ክፍተት በመለየት ክፍተቶችን የመሙላት ተልዕኮ ያዘለ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ አገሮችን የሥጋና የተረፈ ሥጋ የመቀበያ መስፈርት በመገምገምና የምርቱን ተቀባይነት ለማግኘት የሚያስችል መስፈርት የማሟላት ሥራ ወደ ኃላ በመስራት የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የወጪ ንግድን የመጨመር ሥራን አካቶ ይሠራል።

በዚህ ዓመት በየቄራዎች ተመድበው የሚሠሩ 67 ባለሙያዎች እና 4 ሾፌሮች፤ በዋናው መ/ቤትም ዳይሬክተሩን ጨምሮ 4 ባለሙያዎች 1 ሹፌር በጠቅላላም 76 ሠራተኞች በዚህ ዳይሬክቶሬት ሥር ተመድበው በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 7 በውጪ ሀገርና 1 ባለሞያ በሀገር ውስጥ በማስተርስ ዲግሪ፣ 1 በባለሞያ ደግሞ በአገር ውስጥ ለመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ። በተጨማሪም 5 ባለሞያዎች ደግሞ የ6 ወራት የሥጋ ምርመራ ሥልጠና በደ/ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ በመከታተል ተመርቀው ወደ ስራ ገብተዋል። በተጨማሪም 5 ባለሞያዎች ወደ ሌላ ዳይሬክቶሬት በግንቦት ወር 2011 ዓ.ም የተዘዋወሩ ሲሆን 1 ባለሞያ ደግሞ ወደ ዳይሬክቶሬታችን ተዘዋውሯል።

የዚህ ዳይሬክቶሬት ሥራ የአገሪቱ ሥጋ እና የእንስሳት ተረፈ ምርት ኤክስፖርት ተቀባይነት ላይ ጉልህ ድርሻ ስላለው ይህንኑ ተግባር በአግባቡ ለመፈጸም የዳይሬክቶሬቱ ሠራተኞች ተነሳሽነት እና ትጋት እንዲሁም ይህ ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ እንገኛለን።

የዳይሬክቶሬቱ ቢ ኤስ ሲ ዕቅድ የ2ኛውን የዕ ት ዕ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀና ከሚመከታቸው ባለሞያዎች ጋር በውይይት የተሸሻለ ሲሆን ይህንንም ዕቅድ ከዘርፉ ጋር በማዳበር የመጨረሻ ዕቅድ በማድረግ ሥራዎቹ ሲሰሩ ቆይተዋል። በዚህም ረገድ ይህንን 2011 በጀት ዓመት ዕቅድ አስከፈጻሚ የዋናው መ/ቤታ ባለሞያዎችና በየቁራው ለሚገኙ ፈጻሚዎች አውርዶ ካስኬድ በማድረግ እንዲሁም በመፈራረም ወደ ስራ የተገባ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ክንውኑን በየሳምንቱና በየወሩ በመገምገም ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ተችሏል።

ከዚህም በተጨማሪም የ2011 ሁለተኛ ግማሽ ዓመት ጀምሮ ዕቅድ ክለሳ በማድረግ በዚሁ ልክ ስራ የተገባ ሲሆን ይህንንም ዕቅድ ክለሳ ማድረግ ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች ውስጥ በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ያልተጠናቀቁና ታቅደው በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰሩ ሥራዎችን በዚህ በቀጣዩ ግማሽ ዓመት ትኩረት ሰጥቶ ለማከናወን እንዲቻል ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የፕሮጀክት ሥራዎች ጎልተው እንዲታቀዱና የትራንስፎረማሽን አጀንዳ ሥራዎች በተለይም ከግብርና ትራንስፎርኔሽን ኤጀንሲ ጋር በጋራ የሚሰሩ ካሉ በዕቅድ ውስጥ እንዲገቡና እንዲከናወኑ ነው። ከዚህም ሌላ በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ለወጣቶችና ሴቶች ሥራ ፈጠራ ዕድል፣ ለልዩ ድጋፍ ለሚሹ አርብቶ አደር ክልሎችና አካባቢዎችም ጭምር የሚከናወኑ ሥራዎች በዕቅድ ውስጥ ተካተው ድጋፍ ለማድረግ እንዲቻል የዕቅድ ክለሳው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተከልሷል።

በመሆኑም የዓመቱ ክንውን እንደሚከተለው በየግቦቹ የሥራዎችን አፈጻጸም ለማቅረብ ተሞክሯል።

የዓበይት ተግባር አፈጻጸም

ዕይታ፣ ሕብረተሰባዊ/አገራዊ

ግብ **1.** የተገልጋይን የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አሁን ካለበት **80** በመቶ ወደ **90** ማሳደግ፣

- በዚህ ዓመት ውስጥ 2 የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ ተከናውኗል።
- በዚህም መሰረት ጥናቱን በመተንነን ዕርካታን ወደ 90 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ወደ 85 በመቶ ለማድረስ ተችሏል። በዚሁ መሰረት አንድ ቄራ በዝቅተኛ ደረጃ እና አንድ ቄራ ደገሞ በመካከለኛ ደረጃ፣ ሌሎቹ ግን በከፍተኛ ደረጃ በተሰጣቸው አገልግሎት የረኩ መሆኑን በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል።

ግብ **2.** የኤክስፖርት ቄራ የዕርድ መስመር ሰራተኞችንና የቦሌ ስጋ አውራጅ-ጫኝ ሰራተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

- በዚህ ዓመት በተለያዩ ኤክስፖርት ቄራዎች ለሚገኙ 900 የዕርድ መስመር ሠራተኞች ስለ ዘመናዊ የእንስሳት አስተራረድና አገፋፈፍ ሥርዓትና ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተሃድሶ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 883 (644 ወንዶች እና 239 ሴቶች) ሰራተኞችን በማሰልጠን ዕቅዱን 98.1 በመቶ አከናውኗል።
- ቦሌ አየር መንገድ ፍረሽ ፖርት ለሚገኙ 25 የስጋ አውራጅ-ጫኝ ሰራተኞች ሥለ ሥጋ አያያዝና ደህንነት እንዲሁም የግል ንጽህና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ከቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ጋር በመቀኛጀት በዚሁ አግባብ መቶ በመቶ ተከናውኗል።

ግብ **4.** ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መስጠት፣

- በዚህ ዓመት 4 ሚሊዮን እንሰሳት የቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 2.197 (54.9 በመቶ) ሚሊዮን እንሰሳት ለመመርመር ተችሏል፣
- በዓመቱ 3.845 ሚሊዮን እንሰሳት የድህረ ዕርድ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 2.0836 (54.2 በመቶ) ሚሊዮን እንሰሳት መመርመር ተችሏል፣
- በዚህ ዓመት 29490 ቶን ሥጋና 2020 ቶን ተረፈ ሥጋ ምርት ላይ ምርመራ በማድረግ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 16706.93 (56.7 በመቶ) ቶን ሥጋና 1681.72 (83.3 በመቶ) ቶን ተረፈ ሥጋ ላይ ምርመራውን በማካሄድ ወደ ውጪ እንዲላክ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፣
- በዚህ ዓመት 6600 የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለምርቱ ለመስጠት ታቅዶ 8744 (132.4 በመቶ) የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት ተግባር በማከናወን ኤክስፖርቱን ለመደገፍ ተችሏል።

በዚህ ግብ ስር በተለይም የሥጋ ኤክስፖርት ሥራው አፈጻጸም የቀነሰበት ምክንያት የፈጻሚው ችግር ሳይሆን የገበያ ሰንሰለት ችግርና የኤክ/ቄራዎቹ ማናጅመንት የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ማነስ ናቸው። ፈጻሚው የቀረበለትን የቅድመ ዕርድ እንሰሳትና የድህረ ዕርዱን ሙሉ በሙሉ አከናውኖ ምርቱ እንዲላክ ማረጋገጫ በመስጠት የበኩሉን ሚና ተጫውቷል። ነገር ግን ኤክስፖርተሮቹ በዕቅዱ ልክ እንሰሳት የማግኘት ሁኔታና የውጪ ገበያውን ማስፋፋት ባለመቻላቸው እንደዕቅዱ ሊሰራ አልቻለም። በመሆኑም ከሥጋና ወተት ኢንዱ/ል/ኢንስቲትዩትና ከሥጋ ማህበሩ ጋር በጋራ ገበያን ለማስፋፋት ጥረት በመደረግ ላይ ይገኛል፣ ለአብነትም ለጆርዳን እና ለቬትናም አገራት ጥቁያ ቀርቧል። ለማላገሪያም መንግስት ለሚመለከተው መ/ቤትም የተደራጀ የአገራችንን አጠቃላይ የእንሰሳት ጤና አገልግሎት ሁኔታን ያካተተ ሰነድ በመስራት የተላከ ሲሆን ከታችም እንሰሳት አቅርቦት ላይ ትስስር ለመፍጠር በመሰራት ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ እንደ አበርገሌ ኤክ/ቄራ (በተቀባይ አገራት ዕውቅና ባለማግኘቱ ምክንያት) እና እንደ ጅግጅጋ ኤክ/ቄራ (ኮንትሮባንድ በመስፋፋቱ ምክንያት የእንሰሳት ዕጥረትና በማጋጠሙና ከዓዋጪነት ጋር በተያያዘ ምክንያት እንዲሁም በሳውዲ ዕውቅና ያላገኘ በመሆኑ) በዚህ ዓመት ምርታቸውን ባለመላካቸው ሲሆን ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ ከአበርገሌ ኤክ/ቄራን በተመለከተ ሱፐርቪዥን በማካሄድ ያለባቸውን ክፍተት በሪፖርት መልክ ከነመፍትሄው ጋር ያስቀመጥን ሲሆን የማስተካከል ሥራው በማናጅመንቱ የተጀመረ እና ሲጨርሱም በተቀባይ አገራት ዕውቅና እንዲገኙ የግብዣ ደብዳቤ የሚጻፍ ሲሆን፣ የጅግጅጋን ኤክ/ቄራን በተመለከተ እንደዚሁ በሳውዲ ዕውቅና እንዲገኝ በቄራው ማናጅመንት ጋር እየተሰራ ይገኛል።

ዕይታ፣ ሃብት

ግብ 8. የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣

- በዚህ ዓመት በመደበኛ የሚመደበዉን በጀትና አጠቃላይ ሀብት ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል የአፈፃፀምና ሀብት አጠቃቀም ጥምርታ ማሻሻልና የበጀቱን 90 በመቶ ለመጠቀም ታቅዶ የበጀቱን 74 በመቶ ለመጠቀም ተችሏል።

ግብ 9. የሀብት ግኝትን ማሳደግ

- በዚህ ዓመት ሁሉም ኤክ/ቄራዎች ለተሰጣቸው አገልግሎት 2.4 ሚሊዮን ብር ክፍያውን ወደ ባንክ አካውንት ገቢ እንዲያስገቡ ለማድረግ ታቅዶ 1.691 ሚሊዮን (70.5) ብር ገቢ የተደረገ ሲሆን ለክንውኑ በተነጻጻሪ ከፍ ማለት እንደምክንያት የተቀመጠው የአገልግሎት ክፍያውን ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ ባንክ አካውንት እንዲስገቡ ደብዳቤ ከዋናው ዳይሬክቶሬት በመጻፍና ይህ የአገልግሎት ክፍያ ሳይገባ ቢቀር አገልግሎት እንደማያገኙ በማስገንዘብና በአካልም በመገኘት ከቄራው ማናጅመንት ጋር በግልጽ በመወያየት ነው። ከዚህ ባለፈ ግን

ከመከታተልና ከማስረዳት ውጪ በሚ/ር መ/ቤት ደረጃ አስገዳጅ ሥርዓት ባለመቀረጹ ምክንያት አሁንም ችግሩ ያለ ሲሆን እንደመፍትሄ ከመ/ቤታችን ኦዲት ጋር በመተባበር እንዲከፍሉ ግፊት ለማድረግ ተሞክሯል።

- ሀብት ሊያስገኝ የሚችል 1 ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት ታቅዶ በስራ መደራረብና በባለሞያ ዕጥረት ምክንያት ሳይከናወን ቀርቷል።

ዕይታ፣ የውስጥ አሰራር፣

ግብ **10.** ግብ **10.** ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት፣

- በዚህ ዓመት በቄራዎች ሊገኝ የሚችልን አንድ ምርጥ ተሞክሮ ለመለየት፣ ለመቀመርድ እና ለማስፋፋት ዕቅድ ቢያዝም እንደምርጥ ተሞክሮ የሚለይ የሚቀመርና የሚስፋፋ ዳሰሳ ቢደረግም ባለመገኘቱ አልተከናወነም።

ግብ **11.** ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ፣

- በዚህ ዓመት አሁን እየላክን ካሉት አገራት በተጨማሪ 1 አዲስ አንድ አገር ለመላክ የሚያስችል ስምምነት በማድረግ የወጪ ገበያን ለማስፋፋት ታቅዶ በዚህ ረገድ ከኤክስፖርተሮች ጋር በመመካከር ለጆርዳን አገር ሥጋ ለመላክ የሚያስችል ጥያቄና ኤክ/ቄራዎቻችንን መጥተው መጎብኘት እንዲችሉ የግብዣ ደብዳቤ የተላከ ሲሆን ለቬትናምም አገር ሥጋ ለመላክ እንዲቻል ረቂቅ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ተልኳል። ለማላዢያም መንግስት ለሚመለከተው መ/ቤትም የተደራጀ የአገራችንን አጠቃላይ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሁኔታን የሚያሳይና እና የፍሪጎሪፊኮ ኤክ/ቄራን አጠቃላይ ፕሮፋይል ያካተተ ሰነድ ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች እና ከኤክ/ቄራው ጋር በመሆን በማዘጋጀት የተላከ ሲሆን መልስም በመጠባበቅ ላይ እንገናለን።
- የሳውዲ እና የዱባይ የኢንስፔክሽን ቡድንን በመጥራት 1 አዲስ ወደ ስራ የገባ ቄራን በማስገምገም ምርቱን እንዲልክ ለማስቻል ታቅዶ በዳይሬክቶሬት ደረጃ ለ1 አዲስ ቄራ ዕውቅና በመስጠት የተመዘገበ ቢሆንም በባለሀብቱ የአይ ኤስ ኦ (የምግብ ደህንነት ሥርዓት) ዕውቅና ያላገኘ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተቀባይ አገራትን በመጋበዝ ለማስገምገም በዚህ ዓመት ለማከናወን ሳይቻል ቢቀርም በቀጣይ የሚሰራ ይሆናል።
- በዚህ ዓመት ከእንስሳት መድሃኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ጋር በመቀናጀት በስጋ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ጎጂ ቅሪትቶችን (Residues) በማመመርመር 2 የላቦራቶሪ ውጤት ለማውጣትና ለሚመለከታቸው አካላት ለማሰራጨት ታቅዶ 75 ናሙና በመውሰድ እንደ ሙከራ የተሰራ ሲሆን ይህ ስራ ግን ኦፊሺያሊ እንደውጤት ለማውጣትና ወደ ውጪ ለመላክ የራሱ የሆነ ውስንነት ሥላለው ለሚመለከታቸው ተቀባይ አገራት ለመላክ አልተቻለም፣ በመሆኑም ከላቦራቶሪው ማናጅመንትን ከዘርፉ ጋር በመነጋገር ችግሩን በመለየትና መፍትሄ በማስቀመጥ የሚላክበት ሁኔታ እየተመካከርን የምንገኝ ሲሆን ከተባበሩት መንግስታቱ የምግብና እርሻ ድርጅት ጋርም ከዚህ ሥራ ጋር በተያያዘ የቅሪቶችን ምርመራ ዕቅድ ሰነድ (Residiue Monitoring Plan) በመጀመሪያ ደረጃ መሰራት እንዳለበት በመውሰድ እንዲሰራልን ድጋፍ በፕሮጀክቱ በተያዘ ዕቅድ ውስጥ በማስገባት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።
- በዚህ ዓመት ከባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/፣ ከሥጋ አምራች ላኪዎች ማህበር፣ ከመ/ቤታችን የገበያና ግብይት ዘርፍ ወዘተ 4 ቅንጅታዊ ጥምረት በመፍጠር የሥጋ ምርመራና ኤክስፖርት ሥራዎችን ለማሳለጥ ታቅዶ 5 ተከናውኗል። በዚህም ከኦሮሚያ እስልምና ጉዳዩች ምክር ቤት ጋር በጋራ በመሆን አዲስ የተገነባውን ቤንሪኢ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የኦዲት ኢንስፔክሽን ሥራ በመስራት በጋራ ቄራውን የሥራ እና የሀላል **“Certificate of Approval”** የተሰጠው ሲሆን ከስጋ ላኪዎች ማህበር እና ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/ ጋር በመሆን በቄራዎች የተጀመረውን የሥጋ ጥራትና ቅዝቃዜ ሰንሰለት ላይ ክትትል የማድረግ ስራዎች ሶስት ግዜ ተሰርቷል። ከዚህም በተጨማሪ ከስጋ ማህበሩ ጋር በመሆን በቄራዎቹ በነበረው

የትርፍ ሠዓት ክፍያ ችግር ላይ በመወያየት የክትትልና የማስገንዘብ ስራ በመስራት የነበረውን ችግር የጋራ አድርጎ መፍትሄ እንዲፈለግለት የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል። በተጨማሪም የኦሮሚያ እስልምና ጉዳዬች ከፍተኛ ምክር ቤት ዱባይ የሚገኘው የኤምሬት ህላል ዕውቅና ሰጪ ማዕከል የኢንስፔክሽንና የሱፐርቪዝን ጉብኝት የተካሄደበት ሲሆን ይህንንም የተሳካ እንዲሆን ከምክር ቤቱና ከስጋ አምራች ላኪ ማህበር ጋር በጋራ በመስራት የሥጋ ምርቱ የእስልምናና የሸሪዓው ህግ መሰረት ያደረገ መሆኑን በማረጋገጥ ምርቱ በቀጣይ እንዲላክ ለማስደረግ ተችሏል።

- አዲስ ሥራ ለሚጀምሩ ኤክ/ቁራዎች ከሠው ሀብት ጋር በመቀናጀት 15 ባለሞያዎችንና 6 ሹፌሮችን ቅጥር ለማካሄድ ታቅዶ 14 ባለሞያዎች የተቀጠሩ ሲሆን ሹፌሮቹ ግን ባሉት እንዲሰሩ አቅጣጫ በመሰጠቱ ለመቅጠር አልተቻለም።
- በዚህ ዓመት የብሔራዊ የኤስ ፒ ኤስ ኮሚቴ እንደገና በማዋቀር ሥራ ለማስጀመር ታቅዶ ከተባበሩት መንግስታቱ የምግብና እርሻ ድርጅት ሥር በሚገኘው STDF ፕሮጀክት በተያዘው ዕቅድ መሰረት የመጀመሪያ የምክክር መድረክ ተደርጎ ለዘርፉና ለድርጅቱ የስብሰባው ውጤት በሪፖርት መልክ የቀረበ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዘርፉ ደረጃ ይህንን ሥራ የሚያስፈጽምና የሚከታተል አንድ ሐኪም እንደሮካል ፐርሰን ተወክሎ ሥራው ተጀምሯል። በተጨማሪም በሐምሌ ወር ከዓለም ዓቀፉ የንግድ ድርጅት ይህንን ፕሮጀክት ከሚረዳው ክፍል ተወካይ የሚመጣና የብሔራዊ የኤስ ፒ ኤስ ኮሚቴ ምስረታ ስብሰባ ላይ ተገኝተው አቅጣጫ እንዲሰጡ በምግብና እርሻ ድርጅት የኢትዮጵያ ቢሮ ጋር ዕቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል።

ግብ **12.** በሥርዓት ላይ የተመሰረተ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መገንባት፣

- በዚህ ዓመት ኤክስፖርት ቄራዎች በሚኒስትር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ስታንዳርድ የአሰራር ሥርዓት (SOP) እና በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000) ሥርዓት መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ 4 ግዜ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ለማድረግ ታቅዶ ተከናውኗል።
- በዚህ ዓመት 10 በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000-2017/18) ወይም ሃስፕ (HACCP) ሥርዓት በሶስተኛ አካል ዕውቅና ያገኙና በዳይሬክቶሬታችንም ተገምግመው ይሁንታን በማግኘት በትክክል በስርዓቱ መሰረት እተገበሩ ያሉ ቁራዎች ለመደገፍ ታቅዶ 10 ቁራዎች ላይ የተከናውኖ ስምንቱ ሥርዓቱን የሚተገብሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን እነሱም አልነጁም፣ ሞጆ ሞደርን፣ ሃላል፣ አክሽከር፣ ፍሪጎሪፊኮ ቦ/ፉ/ ፣ ሉና፣ አበርገሌ እና ኦርጋኒክ ኤክ/ ቁራዎች ናቸው።
- በዚህ ዓመት የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ላይ በሁለት ዙር ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ ታቅዶ ተከናውኗል።
- በዚህ ዓመት የአዳዲስ የኤክስፖርት ቄራዎች እና የሥጋ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ግንባታ ክንውን በመመሪያና ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ከቦታ መረጣ ጀምሮ 4 ግዜ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ታቅዶ ተከናውኗል።
- በዚህ ዓመት የኤክስፖርት ቄራዎች የሚገኙትን 8 አነስተኛ ላቦራቶሪዎች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ 8 ቄራዎች ላይ በማከናወን 5 ቄራዎች ማለትም ሉና፣ ሞጆ ሞደርን፣ አክሽከር፣ ፍ/ቦ/ፉ/፣ እና ደ/ዘይት ኤልፎራ በትክክል ያላቸውን ላቦራቶሪ እየተጠቀሙ የሚገኙ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹን ግን የላቦራቶሪ ዕቃዎቹን እንዲያሚሉና መሰረታዊ የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ማድረግ እንደሚገባቸው በማስረዳት ክትትልና ድጋፉ በቀጣይ እንደሚቀጥል የጋራ መግባባት ላይ ደርሰናል።
- በዚህ ዓመት በተለዩ 4 የውስጥ/ የውጪ የመልካም አስተዳደር ችግር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመፍታት ታቅዶ 4 በመፍታት የዕቅዱን 100 በመቶ ተከናውኗል። በዚህም ረገድ ከህላል ኤክ/ቄራ ጋር ያጋጠመን የአንድ የባለሞያ የሥራ ላይ ችግር ከድርጅቱ እና ከባለሞያው ጋር በመነጋገርና በመግባባት የተፈታ

ሲሆን የመተህራ ኤልፎራ ኤክ/ቄራ ከባለሞያዎቹ ጋር የነበረውን የሥራ ላይ ችግር በአካል በመገኘትና ሁለቱንም አካላት በማነጋገር ለመፍታት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ የደሞዝና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጋር በተያያዘ ከሚኒስትሩ ጋር በተደረገ ተከታታይ ውይይት የነበረውን ችግር ለመፍታት ተችሏል።

- የጅግጅጋን ኤክ/ቄራን ያለበትን ችግር ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና በመፍታት ኤክስፖርት እንዲጀምር ለማድረግ ታቅዶ ከማናጅመንቱ ጋር የሳውዲን ዕውቅና እንዲያገኝ በቅርበት እየተሰራ ይገኛል።

ግብ **13.** የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽንን ማጎልበት፣

- በዚህ ዓመት የኤክስፖርት ቄራዎችን 200 ሳምንታዊ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ለማቀናጀት ታቅዶ 225 (112.5 በመቶ) ሪፖርቶችን ተሰብስበው ተቀናጅተዋል።
- በዚህ ዓመት 2 የኤክስፖርት ቄራ አገልግሎት ወርሃዊ የበሽታ ግኝት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ለማደራጀትና ለመተንተን እንዲሁም ለማሰራጨት ታቅዶ ተከናውኗል። በዚህም መሰረት ለሙሉ ካርካስ መውደቅ ምክንያቶች ተብለው ተወስዱ በሽታዎችና ሁኔታዎች መካከል ጃውንዲስ፣ መልቲፕል አብሰስ የሚገኙበት ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በብልት (ኦርጋንስ) መውደቅ ምክንያቶች ተብለው የተዘረዘሩ እንደ ኮሶ ዕጭ፣ ሃዳቲድ ሲስት፣ የሳምባ ምች (CCPP, CBPP, Pnemonenea, Pleuritis with adhesion) የጉበት መቆጣት (Hepatitis, Chirrosis Liver fluke, multiple abscesses) የኩላሊት መቆጣት (Nephritis) የመሳሰሉት ናቸው።
- በዚህ ዓመት በሚ/ር መ/ቤታችን ቄብ ሳይት 5 አስፈላጊ መረጃዎችን በመጫን ለተገልጋዩ ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 10 የምንሰራባቸውን ጋይድ ላይኖችን በመጫን ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል።
- በዚህ ዓመት የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን 2 የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት መረጃን በመተንተን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ለማሰራጨት ታቅዶ ተከናውኗል። በዚህም ረገድ በኤርፖርት የሚደርሰው የቅዝቃዜ መጠን ከሞላ ጎደል እስከ 4 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ በመሆኑ ይህንን ወደ 2 ዲ/ሴግሬድ ለማውረድ እንዴት መስራት እንዳለብን በሶስተኛው ሩብ ዓመት በተነጋገርነው መሰረት እየተሰራ ቢገኝም እንደሚፈለገው ወደ 2 ለማውረድ ያልተቻለበት ሁኔታ እንዳለ ለመገምገም የተቻለ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥጋ ማጓጓዣ መኪኖቹን ማቀዝቀዣ መሳሪያን ካሊብሬት እንዲያስደረጉ ለቄራው ማናጅመንት አስገንዝበናል።
- በዚህ ዓመት 300 ጥራዝ የዓለም አቀፍ የጤና ሰርተፊኬት ለማሳተምና ለማሰራጨት የታቀደ ሲሆን ተከናውኗል።

ግብ **14.** የዳይሬክቶሬቱን የአሰራር ስርአቶች ውጤታማነት ማሳደግ፣

- በዚህ ዓመት የሥጋ ምርመራና ሀይጂን ደንብ በማርቀቅ ለዘርፉ ለማቅረብ ታቅዶ በሂደት (70 በመቶ) ላይ ያለ ሲሆን ለመዘግየቱም ምክንያት የዋናው ዓዋጅም ሥራ ባለመጠናቀቁ እና የባለሞያ እጥረት ማለትም ካሉት 5 ሐኪሞች ሁለቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ት/ህርት የሄዱ እና አንድ ሐኪም ደግሞ ሙሉ ግዜውን የ HEARD ፕሮጀክት ስራ እንዲሰራ በመደረጉ ቀጥሎም በአራተኛው ሩብ ዓመት ውስጥ ጡረታ በመውጣቱ ሥራዎች በመደራረባቸው ነው።
- በዚህ ዓመት የጋማ ከብት ዕርድ ምርመራን ለማድረግ የሚያስችል ኤስ ኦ ፒ በማዘጋጀትና በማዳበር ወደ ሥራ ለማስገባት ታቅዶ ወደ ስራ የተገባ ቢሆንም (90 ከመቶ ቢከናወንም) በሥራ መደራረብና የጋማ ከብት ቄራው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እንዳይሰራ ዕገዳ በማደረጉ ምክንያት ለመጨረስ አልተቻለም።

- በዚህ ዓመት ሌሎች 5 ልዩ ልዩ የዕርድ መስመር ኤስ ኦ ፒ ለማዘጋጀት ታቅዶ 6 በማዘጋጀት (120 በመቶ) ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ሲሆን እነሱም የቅድመ ዕርድ ምርመራ፣ የባራኪ፣ የገፋፊ፣ የሆድ ዕቃ አውጪ፣ የኦርጋኒክ አሲድ ረጪና የማቀዝቀዣ ክፍል መስመር ሥራዎች ኤስ ኦ ፒ ናቸው።
- በዚህ ዓመት በተለየ 4 የውስጥ/ የውጪ የመልካም አስተዳደር ችግር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመፍታት ታቅዶ 3 ችግሮችን በመፍታት የዕቅዱን 100 በመቶ ተከናውኗል። በዚህም ረገድ ከሀላል ኤክ/ቄራ ጋር ያጋጠመን የአንድ የባለሞያ የሥራ ላይ ችግር ከድርጅቱ እና ከባለሞያው ጋር በመነጋገርና በመግባባት የተፈታ ሲሆን የመተሀራ ኤልፎራ ኤክ/ቄራ ከባለሞያዎቹ ጋር የነበረውን የሥራ ላይ ችግር በአካል በመገኘትና ሁለቱንም አካላት በማነጋገር ለመፍታት ተችሏል። ከዚህም በተጨማሪ ከኦርጋኒክ ኤክ/ቄራ ባለሞዎች ዕርስ በዕርስ ያለመግባባት ችግራቸውን በተከታታይ ለ 2 ግዜ በመነጋገር ተፈትቶ በጥሩ መንፈስ ሥራ እየተሰራ ይገኛል።
- በዚህ ዓመት የብቃት ማረጋገጫ መስጫ መስፈርትን በማሻሻል ለበላይ አካል ለማቅረብ ታቅዶ ስራው የተጀመረ ቢሆንም (50 በመቶ) በባለሞያ ዕጥረትና በስራ መደራረብ ምክንያት ለመጨረስ ባይቻልም በተለይም ከተባበሩት መንግስታቱ የምግብና እርሻ ድርጅት ጋርም ከዚህ ሥራ ጋር በተያያዘ ድጋፍ ተደርጎ እንዲሰራልን ተጠይቆ መልስ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

ዕይታ፣ መማማርና ዕድገት፣

ግብ **16.** የአመራርና ፈፃሚ እወቀት፣ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ፣

- በዚህ ዓመት ለ 55 ነባር ኤክስፓርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የተህድሶ ሥልጠና ለመሰጠት ታቅዶ በሥራ መደራረብ ምክንያት ለማከናወን አልተቻለም፣
- በዚህ ዓመት ለ 10 ላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች ስለ ላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች ከሰበታ ላቦራቶሪ ጋር በመተባበር የተህድሶ ሥልጠናው እንዲሰጣቸው ለማድረግ ቢታቀድም በሥራ መደራረብ ምክንያት ለማከናወን አልተቻለም፣
- በዚህ ዓመት 25 የሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች የ6 ወር ሥልጠና በመስጠት ዕውቅና ያገኙ ሥጋ መርማሪዎች ለማድረግ ታቅዶ 5 ባለሞያዎችን ለማሰልጠን የተቻለ ሲሆን ቀሪ ባለሞያዎችን ለማሰልጠን በጀት ከ ኀርድ ፕሮጀክት ጋር የተያዘ ቢሆንም ፕሮጀክቱ ሥራ ለመጀመር የዘገየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቀጣይ በጀት ዓመት የሚከናወን ይሆናል።
- በዚህ ዓመት ስለ ጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት. ፋይዳ ለ 60 የኤክ/ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ 30 ባለሞያዎች (50 በመቶ) ሥልጠናውን ተሰጥቷል። ክንውኑ ያነሰበት ምክንያት እንደ አበርገሌ፣ አዳሚ ቱሉ እና መትሃራ ኤክ/ቄራዎች ውስጥ ያሉ ባለሞያዎች ከርቀት፣ ከስራ መብዛትና ብዙዎቹ በአሁኑ ሰዓት የዓመት ዕረፍት እንዲሁም በትምህርት ላይ በመሆናቸው ነው።

ግብ. **17.** የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም አቅም ማሳደግ፣

- ለ11 ኤክስፖርት ቄራዎች 22 ደስክ ቶፕ ኮምፑትር፣ ፕሪንተርና ላብቶፕ በመግዛት ለማሰራጨት ቢታቀድም 3 ያገለገሉ ደስክ ቶፖችና 6 ያገለገሉ ላብቶፖች እንዲሁም 3 ፕሪንተሮች ከዘርፋና ሌሎች ፕሮጀክቶችና ዳይሬክቶሬቶች ጋር በመነጋገር ለሚሟላት ተችሏል።

ግብ **18.** በቢሮ ያሉ ሥራ ከባቢዎችን ምቹ ማድረግ፣

- በዚህ ዓመት በቢሮ ውስጥ የሚገኙ አላስፈላጊ የተበላሹ ዕቃዎችንና የተከማቹ ወረቀቶችን በ 2 ዙር ለማስወገድ ታቅዶ የተከናውኗል።

ከዕቅድ ውጪ የተሰሩ ሥራዎች፣

- የቬርዴ ቢፍ ፕሮሴሲንግ የአፍ ተዕግር በሽታን ከማድለቢያ ጣቢያ ነጻ ለማድረግ የጀመረውን እንቅስቃሴ ለመደገፍና ለማረጋገጥ ከዘርፉ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ከ 4 ዳይሬክቶሬቶችና ከሰበታ ላብራቶሪ አንድ አንድ ባለሞያ በመስጠት አጥኚ ግብር ሃይል ተቋቋሞ ሥራውን ሰርቷል። በመሆኑም በዚህ ረገድ ከሰበታ ላቦራቶሪ ጋር በመቀናጀት 303 የደም ናሙናዎች በመውሰድ በፋርሙ ያለውን የአፍ ተዕግር በሽታ 15 በመቶ ያህል መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን በአሁን ፋርሙን ከበሽታ ነጻ ነው ለማለት አያስደፍርም። በሂደት ግን የሚከተሉት ተግባራት ከተከናወኑ እንደገና ሊታይ የሚችል የሚችል መሆኑን አስቀምቷል።
    - ሚ/ር መቤቱ ያወጣውን የአፍ ተዕግር በሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ በተለይም በኤክስፖርት ኮሪዶር ተግባራዊ ቢያደረግ፣
    - የፋርሙን ባዮስኩሪቲን ማጠናከር፣
    - እንሰሳት በሚገዙበት አካባቢ ያለውን የበሽታ ስርጭትና ቁጥጥር በቅርበት መከታተል፤ ዕገዛም የሚያስፈልግ ከሆነ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
    - አላስፈላጊ የሰውና የመኪና ጎብኚዎችን ወደ ፋርሙ የመግባት ሁኔታን መቆጣጠር፣ መቀነስ።
    - የመኪና ጎማና የሰው ዕግር ዲስኢንፌክታንትስ በአስፈላጊ ቦታዎች ላይ በመስራት እንዲጠቀሙ ማድረግ።
- ቤንሮኢ የተባለ በአዋሽ መልካሳ የሚገኝ አንድ አዲስና በጣም ዘመናዊ ኤክስፖርት ቄራ አጠቃላይ ፍተሻ በማድረግ ዕውቅና በዳይሬክቶሬት ደረጃ የተሰጠውና የተቀባይ አገራትን ዕውቅና እንዲገኝ ለማድረግ እንዲቻል የምግብ ደህንነት (አለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000 2005) ሥርዓት በመተግበር ሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ይህንን ጨርሶ ዕውቅናውን ሲያገኝ የተቀባይ አገራት መጥተው እንዲጎበኙትና ዕውቅና ሰጥተው ምርቱን እንዲልክ የሚደረግ ይሆናል።
- 10 ኤክ/ቄራዎች (አበርገሌን፣ ሀሺምንና ጅግጅጋ ኤክ/ቄራዎችን ሳያካትት) የ2019 ዓመት የሥራ ፈቃዳቸው በተከታታይ በተደረጉ የመስክ ምልከታዎች መሰረት የታደሰላቸውና ይህንንም ለተቀባይ አገራት በኢሜይል እንዲውቁት በማድረግ ኤክስፖርቱ ያለምንም ዕንከን እንዲሳለጥ ለማድረግ ተችሏል።
- ለ4 አዲስ ኦፋል ላኪዎች እና ለ 8 አዲስ ሥጋ ላኪ ድርጅቶች ከተለያዩ ኤክስፖርት ቄራዎች ጋር ባደረጉት የውል ስምምነት መሰረት የንግድ ፈቃድ አውጥተው እንዲሰሩ መስፈርቱ መሰረት አድርጎ በመገምገም ለንግድ ሚኒስቴር የድጋፍ ብቃት ማረጋገጫ ደብዳቤ ተጽፎላቸው የበኩላቸውን ኤክስፖርት እንዲደርጉ ሁኔታዎችን አመቻችተናል።

ዋና ዋና ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትዎች፣

- ለዳይሬክቶሬት ለ2011 በጀት ዓመት የሚሆን በቂ በጀት ባለመመደቡ ምክንያት ኤክስፖርቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ደርሷል። ይህም መገለጫውና ምክንያቱ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጋር ተያይዞ ለ9 ወራት ያልተከፈለ በመሆኑ ሲሆን እንደመፍትሄ ክቡር ሚኒስትሩ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በጉዳዩ ላይ በማነጋገር ከዚህ በፊት እንዳይከፈል የተደረገውን በማስነሳት እንዲከፈል ተደርጓል፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ ለ2012 በጀት ዓመት ይህንን ችግር ሥርዓት ባለው መንገድና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም በፈቀደው አግባብ ለመክል ያመች ዘንድ የአከፋፈል ስርዓት አጥንቶ ያቀርብ ዘንድ አንድ ኮሚቴ የተዋቀረ ሲሆን ሥራውንም በመስራት አቅርቦ ከሰቪል ሰርቪስም ኮሚሽን ይሁንታን በማግኘቱ በመጨረሻ ወር ተከፍሏል።
- ከዚህ በፊት ማለትም 2010 ለዳይሬክቶሬቱ ይመደብ የነበረው የሞባይል ካርድ በመቋረጡ ምክንያት ከኤክ/ቄራዎች ጋር ከስራ ሰዓት ውጪ በተለይም ቅዳሜና እሁድ በመገናኘት ለመደገፍም ሆነ መረጃ

ለመለዋወጥ አልተቻለም። ሆኖም በየኤክስፖርት ያሉ አስተባባሪዎችና ዳይሬክተሩ ከደሞዛቸው በመቀነስ የሞባይል ካርድ በመግዛት የመንግስትን ስራ እየደገፉ የሚገኙ ሲሆን ሚ/ር መ/ቤቱ ይህንን የሥራ ጸባይ በማየት ከበፊቱም በተሻለ ሁኔታ ሞባይል ካርድ ምደባ በማድረግ ኤክስፖርቱ እንዲሳለጥ ቢያደርግ፣ የጣቢያ አስተባባሪዎች የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲያገኙ የኢቪዶዮ መሳሪያ ቢመደብላቸውና ሳምታዊ ሪፖርት በወቅቱ የሚላክበት ሁኔታ ቢመቻች፣

- በየቁራዎች የተንሰራፋውን የሰርቪስ መኪና ችግር ለመቅረፍ እንዲያስችል ለኦርጋኒክና ለሉና ኤክ/ቁራዎች የሚመደቡ መኪናዎችን ከሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶች ጋር በመነጋገር የተመደበ ቢሆንም የኦርጋኒኩ መኪና ከ 1 ሳምንት ሥራ ቦሃላ ያገለገለ መኪና ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በመበላሸቱ ተጎትቶ መጥቶ ወደ ገራዥ የገባ ሲሆን ለሉና ግን ሹፌር ባለመቀጠሩ መኪናውን ወጪ ለማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም ቢያንስ 4 ሹፌሮች እንዲቀጠሩ ከትራንስፖርትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ጋር ስምምነት በመድረስ ለሚመለከተው የሰው ሃይል ጥያቄው እንዲቀርብ የተስማማን ቢሆንም አልተሳካም፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም የመትሃራ፣ የአልኑጁምና የሞጆ ሞደርን ኤክ/ቁራዎች እንደዚሁ የሰርቪስ መኪና የሌላቸውና በእግርና በባጃጅ እንደዚሁም ባለሀብቱን በማስቸገር ወደ ሥራ ለመውጣትና ለመግባት ተገደዋል። በመሆኑም ክቡር ሚኒስትሩ ከዚህ በፊት በእንሰሳት ጤና እና ልማቱን ዘርፎችን ሲገመግሙ ባስቀመጡት አቅጣጫ መሰረት ሁሉም ቁራዎች የሠርቪስ መኪና እንዲመደብላቸው ቢደረግ።
- የበረዶ ቤት ልብስ እና የራስ ቅል መከላከያ ሄልሜት በግዢ በኩል ለ2010 በጀት ዓመት ለመግዛት በገበያ ላይ ያልተገኘ መሆኑንና ዳይሬክቶሬቱም ይህንን ችግር በመጥቀስ በወቅቱ የመፍትሄ ዓመራር እንዲሰጥበት ለዘርፋችን ያቀረበ ሲሆን ዘርፉም ለሚኒስትር ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ለአፈጻጸም የተመራ ቢሆንም እስካሁን ዛሬ ነገ እየተባለ ውሳኔ ሳይሰጥ የቀረ ስለሆነ በዘርፉ በኩል ክትትል ተደርጎ የውሳኔ ዓመራር ቢሰጥልን፣ አሁንም በግዢ በኩል በሰኔ ወር ውስጥ በጣም በርካታ ግዢዎች የተፈጸሙ ቢሆንም በዳይሬክቶሬታችን ላሉ ባለሞያዎች የደንብ ልብስ፣ ጽዳት ዕቃዎቸና ሌሎች አስፈላጊ የቢሮ አላቂ ዕቃዎች ለሁላችንም ያልተዳረሰበት ሁኔታ በመኖሩ የትራንፖርትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት መፍትሄ ቢሰጥበት‹።

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| ህብረተሰባዊ/ ሃገራዊ 30 በመቶ | ግብ 1. የተገልጋይ እርካታን ማሳደግ | በዳይሬክቶሬቱ በተሠጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የረኩ ተገልጋዮች (ኤክስፖርት ቁራዎች) | የተገልጋይን የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ አሁን ካለበት 80 በመቶ ወደ 90 ማሳደግ | የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | የተጠና ጥናት በቁጥር | 2 | 5 | 1 | 2 | 1 | 2 | | 100 | 100 | |
| | | | | ጥናቱን በመተንን ዕርካታን ወደ 90 ማድረስ | በመቶኛ | 90 | 4 | - | 90 | 85 | 85 | 94.4 | 94.4 | 94.4 | |
| | ግብ 2. የተገልጋይ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | የተሳለጠና ደህንነቱ የተጠበቀ የሥጋ አመራረት ሂደት ውስጥ ተሳትፎአቸውና ተጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ተገልጋዮች | የኤክስፖርት ቁራ የዕርድ መስመር ሰራተኞችንና የቦሌ ስጋ አውራጅ-ጫን ሰራተኞች ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ | በተለያዩ ኤክስፖርት ቁራዎች ለሚገኙ የዕርድ መስመር ሠራተኞች ስለ ዘመናዊ የእንሰሳት አስተራረድና አገፋፈፍ ሥርዓትና ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ ግንዛቤ እንዲጨብጡ የተሃድሶ ሥልጠና መስጠት፣ | የሠልጠኘ ብዛት በቁጥር | 900 | 8 | 250 | 900 | 268 | 883 | 107.2 | 98.1 | 98.1 | |
| | | | | ቦሌ አየር መንገድ ፍረሽ ፖርት ለሚገኙ 25 የስጋ አውራጅ-ጫን ሰራተኞች ሥለ ሥጋ አያያዝና | የሠልጠኘ ብዛት በቁጥር | 25 | 4 | 25 | 25 | 25 | 25 | 100 | 100 | | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚ ህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | ደህንነት እንዲሁም የግል ንጽህና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት፣ | | | | | | | | | | | |
| | ግብ 4. የእንሰሳት ና አሳ ግብአትና ምርት ጥራት ቁጥጥር ማሻሻል | የተሻሻሉ ደህንነቱና ጥራቱ ተጠብቆ የተመረተ ሥጋና ተረፈ ሥጋ፣ | ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽን ና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት መስጠት | የቅድመ ዕርድ ምርመራ ማካሄድ | `በሺህ ቁጥር | 4000 | 2 | 800 | 4000 | 567.25 | 2197.06 | 70.9 | 54.9 | 54.9 | |
| | | | | ዳልጋ ከብት | `በሺህ ቁጥር | 85 | | 20 | 85 | 5.3 | 24.1 | 26.5 | 28.4 | 28.4 | |
| | | | | በግና ፍየል | `በሺህ ቁጥር | 3915 | | 780 | 3915 | 561.95 | 2172.96 | 72 | 55.5 | 55.5 | |
| | | | | የድህረ ዕርድ ምርመራ ማካሄድ | `በሺህ ቁጥር | 3845 | 3 | 770 | 3845 | 540.18 | 2083.63 | 70.2 | 54.2 | 54.2 | |
| | | | | ዳልጋ ከብት | `በሺህ ቁጥር | 85 | | 20 | 85 | 5.3 | 23.9 | 26 | 28.1 | 28.1 | |
| | | | | በግና ፍየል | `በሺህ ቁጥር | 3760 | | 750 | 3760 | 534.88 | 2059.73 | 75.3 | 55 | 55 | |
| | | | | ምርመራ የተካሄደበት ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት | በቶን | 31510 | 3 | 6030 | 31510 | 4855 | 18388.65 | 80.5 | 58.4 | 58.4 | |
| | | | | ምርመራ የተካሄደበት የሥጋ ምርት | በቶን | 29490 | | 5520 | 29490 | 4533 | 16706.93 | 82.1 | 56.7 | 56.7 | |
| | | | | ምርመራ የተካሄደበት የተረፈ ሥጋ ምርት | በቶን | 2020 | | 510 | 2020 | 322 | 1681.72 | 63.1 | 83.3 | 83.3 | |
| | | | | ለምርቶቹ የተሰጠ የጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት | በቁጥር | 6600 | 3 | 2200 | 6600 | 2351 | 8744 | 106.9 | 132.4 | 132.4 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| ሃብት (10 በመቶ) | ግብ 8. የሃብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | | የዳይሬክቶሬቱን የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | የበጀት አጠቃቀምን ከነበረበት 80 በመቶ ወደ 90 በመቶ ማሳደግ፣ | በመቶኛ | 90 | 4 | | 90 | | 72 | 72 | 72 | 72 | |
| | ግብ 9. የሀብት ግኝትን ማሳደግ | በተለያዩ ሥራዎች በመስራት የተገኘ ሀብት | የሃብት ግኝት ማሳደግ | በበጀት ዓመቱ ኤክ/ቂራዎች የአገልግሎት ክፍያ ወደ ባንክ አካውንት እንዲስገቡ ማድረግ፣ | በሚሊዮን ብር | 2.4 | 4 | 0.8 | 2.4 | 0.422 | 1.691 | 52.8 | 70.5 | 70.5 | |
| | | | | ሀብት ሊያስገኝ የሚችል 1 ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማዘጋጀት፣ | የተዘጋጀ ፕሮፖሳል | 1 | 2 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| የዉስጥ አሰራር (45 በመቶ) | ግብ 10. ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት | ተለይቶና ተቀምሮ የተስፋፋ ምርጥ ተሞክሮ፣ | በቁራዎች ሊገኝ የሚችልን ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት አሰራርን ማጎልበት፣ | የተለየ ምርጥ ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | 0.5 | | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | የተቀመረ ምርጥ ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | 0.5 | | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | የተስፋፋ ምርት ተሞክሮ | በቁጥር | 1 | 0.5 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | ግብ 11. ቅንጃዊ | ያደገና የተጠናከረ | ቅንጅታዊ አሰራርን ማሳደግ | አሁን እየላክን ካሉት አገራት በተጨማሪ 1 አዲስ አገር ለመላክ | የተጨመረ አዲስ አገር | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0.5 | 0 | 50 | 50 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚ ህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | አሰራርን ማሳደግ | ቅንጅታዊ አሰራር | | የሚያስችል ስምምነት በማድረግ የወጪ ገበያን ማስፋፋት፣ | | | | | | | | | | | |
| | | | | የሳውዲ እና የዱባይ የኢንስፔክሽን ቡድንን በመጥራት 1 አዲስ ወደ ስራ የገባ ቄራን በማስገምገም ምርቱን እንዲልክ ማስቻል፣ | ምርታቸውን ለመላክ የቻሉ ቄራዎች ብዛት | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | ከእንሰሳት መድሃኒትና መኖ ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ ጋር በመቀናጀት በስጋ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ጎጂ ቅሪትቶችን (Residues) በማመመርመር የላቦራቶሪ ውጤት ማውጣትና ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፣ | የወጣ የላቦራቶሪ ወጤት በሰነድ | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 100 | 50 | 50 | |
| | | | | ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ማለትም ከሥጋና ወተት ኢ/ል/ኢ/፣ ከሥጋ አምራች ላኪዎች ማህበር፣ ከመ/ቤታችን የገበያና ግብይት ዘርፍ ቅንጅታዊ ጥምረት | የተፈጠረ ቅንጅታዊ ትስስር የተራ | 4 | 3 | 1 | 4 | 1 | 5 | 100 | 166.7 | 125 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | በመፍጠር የሥጋ ምርመራና ኤክስፖርት ሥራዎችን ማሳለጥ፣ | ሥራ ብዛት | | | | | | | | | | |
| | | | | አዲስ ሥራ ለሚጀምሩ ኤክ/ቄራዎች ከሠውሀብት ጋር በመቀናጀት 15 ባለሞያዎችንና 6 ሹፌሮችን ቅጥር ማካሄድ፣ | 21 የተቀጠሩ ባለሞያዎችና ሹፌሮች | 21 | 2 | 21 | 21 | 14 | 15 | 71.4 | 71.4 | 71.4 | |
| | | | | የብሔራዊ የኤስ ፒ ኤስ ኮሚቴ እንደገና በማዋቀር ሥራ ማስጀመር | የተዋቀረና ሥራ የጀመረ ኮሚቴ | 1 | 2 | - | 1 | 0.5 | 1. | | 100 | 100 | |
| | ግብ 12. የክትትል ግምገማና ድጋፍ ስርአትን ማጠናከር | ወቅታዊ ድጋፍ፣ ክትትልና ግምገማ ተደርጎለት የተጠናከረ የኢንስፔክሽንና የሰርተፊኬሽን አገልግሎት፣ | በሥርዓት ላይ የተመሰረተ ግምገማ፣ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ በመስጠት እያደገ የሚሄድ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን | ኤክስፖርት ቄራዎች በሚኒስትር መ/ቤቱ ተዘጋጅቶ በተላከላቸው ስታንዳርድ የአሰራር ሥርዓት (SOP) እና በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000) ሥርዓት መሰረት ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ክትትል፣ ድጋፍና ቁጥጥር (ኦዲት) ማድረግ፣ | በክትትልና ቁጥጥር ግዜ | 4 | 5 | 1 | 3 | 1 | 3 | 100 | 100 | 75 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | አገልግሎት መገንባት፣ | በአለም አቀፉ የምግብ ደህንነት ማኔጅመንት (ISO 22000-2017/18) ወይም ሃስፐ (HACCP) ሥርዓት በሶስተኛ አካል ዕውቅና ያገኙና በዳይሬክቶሬታችንም ተገምግመው ይሁንታን አግኝተው በትክክል በስርዓቱ መሰረት እየተገበሩ ያሉ ቁራዎች፣ | ኤክ/ቁራ ዎች ብዛት | 10 | 3 | 4 | 10 | 3 | 75 | 80 | 80 | 80 | |
| | | | | የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቁራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ፣ | የተደረገ ክትትልና ቁጥጥር፣ | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | የአዳዲስ የኤክስፖርት ቁራዎች እና የሥጋ ተረፈ ምርት ማቀነባበሪያ ግንባታ ክንውን በመመሪያና ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን ከቦታ መረጣ ጀምሮ መከታተል እና መቆጣጠር | በክትትል ግዜ | 4 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | ኤክስፖርት ቄራዎች የሚገኙትን አነስተኛ ላቦራቶሪዎች የሚፈለግባቸውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤ | ክትትልና ድጋፍ የተደረገላቸው የቄራ ላቦራቶሪዎች ብዛት | 8 | 2 | 2 | 8 | 2 | 10 | 100 | 125 | 125 | |
| | | | | ከዚህ በፊት በተለዩ የኪራይ ሰብሳቢነት አዝማሚያዎችን በመከታተል የማክሰሚያ ሥልቶችን ተግባራዊ ማድረግ | ተግባራዊ የተደረጉ የማክሰሚያ ስልቶች በቁጥር | 4 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | የጅግጅጋን ኤክ/ቄራን ያለበትን ችግር ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀትና በመፍታት ኤክስፖርት እንዲጀምር ማድረግ፣ | ሥራ መስጀመር | | 1 | 1 | 1 | 0.5 | 0.5 | 50 | 50 | 50 | |
| | ግብ 13.የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽ | የጎለበተ የመረጃአቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽን | የመረጃ አቅርቦት ስርጭትና ኮምኒኬሽንን ማጎልበት | የኤክስፖርት ቄራዎችን ሳምንታዊ ወርሃዊ እና የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ማቀናጀት | ተሰብስበው የተቀናጁ ሪፖርቶች በዛት | 200 | 2 | 50 | 200 | 71 | 225 | 142 | 112.5 | 112.5 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ን ማጎልበት | | | የኤክስፖርት ቄራ አገልግሎት ወርሃዊ የበሽታ ግኝት ሪፖርቶችን በመሰብሰብ ማደራጀትና መተንተን | ተሰብስቦ የተደራጀ መረጃ | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | የተተነተነው የኤክስፖርት ቄራ የበሽታ ግኝት መረጃ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት | የተሰራጨ መረጃ | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | በሚ/ር መ/ቤታችን ዌብ ሳይት አስፈላጊ መረጃዎችን በመጫን ለተገልጋዩ ተደራሽ ማድረግ | የተጫኑ መረጃዎች ብዛት | 5 | | 2 | 5 | - | 10 | - | 200 | 200 | |
| | | | | የሥጋ ቅዝቃዜና ጥራትን በተመለከተ ከቄራዎች ጀምሮ እስከ ቦሌ ፍረሽ ፖርት ድረስ የሚገኘውን የጥራት ሁኔታ ለማሻሻል የተዘረጋውን የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት መረጃ በመተንተን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሰራጨት፣ | ተተንትኖ የተሰራጨ መረጃ | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 100 | 100 | 100 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚ ህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ግብ 14፡ የሴክተር አሰራር ስርዓቶች ን በተሟላ መልኩ መዘርጋት ና በቀጣይነ ት ማሻሻል | በተሟላ መልኩ የተዘረጉና በቀጣይነት የሚሻሻሉ የሴክተር አሰራር ስርዓቶች፣ | የዳይሬክቶሬቱ ን የአሰራር ስርአቶች ውጤታማነት ማሳደግ | የዓለም አቀፍ የጤና ሰርተፊኬት ማሳተምና ማሰራጨት | ጥራዝ ብዛት | 300 | 2 | - | 300 | - | 300 | | 100 | 100 | |
| | | | | የሥጋ ምርመራና ሀይጂን ደንብ በማርቀቅ ለዘርፉ ማቅረብ | የቀረበ ደንብ | 1 | 1 | - | 1 | - | 0.5 | - | 50 | 50 | |
| | | | | የጋማ ከብት ዕርድ ምርመራን ለማድረግ የሚያስችል ኤስ ኦ ፒ በማዘጋጀትና በማዳበር ወደ ሥራ ማስገባት፣ | የተዘጋጀ ኤስ አ ፒ | 1 | 0.5 | - | 1 | 0.2 | 0.9 | | 90 | 90 | |
| | | | | ሌሎች ልዩ ልዩ የዕርድ መስመር ኤስ ኦ ፒ ማዘጋጀት | የተዘጋጁ ኤስ ኦፒ ብዛት | 5 | 3 | 3 | 5 | 4 | 6 | 133 | 120 | 120 | |
| | | | | በተለዩ የውስጥና የውጪ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መፍታት | የተፈቱ ችግሮች ን ከሚመለ ከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መፍታት | 4 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 | 100 | 100 | 100 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | | | | የብቃት ማረጋገጫ መስጫ መስፈርትን በማሻሻል ለበላይ አካል ማቅረብ | የቀረበ ሰነድ | 1 | 1 | | 1 | 0 | 0.5 | | 50 | 50 | |
| መማማርና እድገት (15%) | ግብ 16 የአመራርና ፈፃሚ እወቀት፣ክህሎትና አመለካከት ማሳደግ | እወቀቱ፣ክህሎትና አመለካከቱ ያደገ ኣመራርና ፈጻሚ | የአመራር እና ፈጻሚ ክህሎት እና አመለካከትን ማሳደግ፣ | ለነባር ኤክስፖርት ቄራ ሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች በስጋ ምርመራ ዙሪያ የተሀድሶ ሥልጠናው መሰጠት ማድረግ፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 55 | 2 | 55 | 55 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | ለላቦራቶሪ ቴክኒሻኖች ስለ ላቦራቶሪ ምርመራ ዘዴዎች ከሰበታ ላቦራቶሪ ጋር በመተባበር የተሀድሶ ሥልጠናው እንዲሰጣቸው ማድረግ፣ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 10 | 1 | 10 | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| | | | | የሥጋ መርማሪ ባለሞያዎች የ6 ወር ሥልጠና በመስጠት ዕውቅና ያገኙ ሥጋ መርማሪዎች ማድረግ | የሠልጠኝ ብዛት በቁጥር | 25 | 2 | - | 25 | - | 5 | - | 20 | 20 | |
| | | | | በሞያ ስነምግባርና ስለ ጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ፋይዳ ለባለሞያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት፣ | የባለሞያ ብዛት | 60 | 3 | 60 | 60 | 30 | 30 | 50 | 50 | 50 | |

| ዕይታ | የተቋም ስትራቴጂክ ግብ | የግብ አመላካች | የስራ ክፍሉ ዓመታዊ ግብ | ግቡን ለማሳካት የተቀመጡ ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ ኢላማ | ክብደት | ዕቅድ | | ክንውን | | ንጽጽር | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | የዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | በዚህ ሩብ ዓመት | እስከዚህ ሩብ ዓመት | ከዓመቱ | |
| | ግብ. 17. የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት አጠቃቀም አቅም ማሳደግ፣ | አቅርቦቱና የአጠቃቀም አቅሙ ያደገ የኢንፎርሜሽንኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ | የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት አጠቃቀም አቅም ማሳደግ፣ | ለ11 ኤክስፖርት ቁራዎች ደስክ ቶፕ ኮምፑትር፣ ፕሪንተርና ላብቶፕ በመግዛት ማሰራጨት | ተገዝቶ የተሰራጨ ብዛት | 22 | 4 | | 22 | 12 | 12 | 0 | 54.5 | 54.5 | |
| | ግብ 18. ለስራምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን ማሻሻል፣ | የተሻሻሉና ለሥራ ምቹ የሆኑ ከባቢያዊ ሁኔታ፣ | በቢሮ ያሉ ሥራ ከባቢዎችን ምቹ ማድረግ፣ | በቢሮ ውስጥ የሚገኙ አላስፈላጊ የተበላሹ ዕቃዎችንና የተከማቹ ወረቀቶችን ማስወገድ፣ | በ 2 ዙር የተወገዱ የተበላሹ ዕቃዎችና ወረቀቶች | 2 | 3 | 1 | 2 | 0.5 | 2 | 0.5 | 100 | 100 | |